በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-197405

ቀን፡- 29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. የቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 አስተዳደር ጽቤት } አልቀረቡም

2ኛ. የቂ/ክ/ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽቤት }

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት- ነ/ፈጂ ወይንሸት እንድሪስ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 247606 ግንቦት 17 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡አመልካቾች በስር በፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ በኢትዮጵያ ጅቡቲ መንግስት መካከል በተደረገው ዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በተቋቋመ የሁለቱ መንግስታት ንብረት የሆነ የዓለም አቀፍ ድርጅት ሲሆን በሁለቱ መንግስታት የመሬት ይዞታ ተለክቶ ተሰጥቶታል፡፡በአዋጅ ቁ. 47/67 አንቀጽ 43 እና 5 (3) መሰረት የዓለም አቀፍ ድርጅት ቦታ የማይወረስ ሲሆን የተጠሪ ቤትና ይዞታ ያልተወረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤም በወቅቱ ከነበረው የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተሰጥቶታል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ለአጣዳፊ ስራ ለሚፈልጉ ሰራተኞች ቤት ስለሚሰጥ በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 159 ለአቶ ነጋሽ ተፈራ ሰጥቶ ነበር፡፡የእኚህ ግለሰብ የስራ ግንኙነት በሞት ምክንያት የተቋረጠ ሲሆን በህይወት እያለ ቤቱን ከሕግና ከድርጅቱ አሰራር ውጪ ኃ/ማሪያም አስራት ለተባለ ሰው አስተላልፈው አቶ ኃ/ማሪያም አስራት ደግሞ ቤቱን የቀበሌ በማስመሰል በወቅቱ ከአመልካቾች ጋር ውል ተዋውሏል፡፡ግለሰቡ አሁን በህይወት የሌለ ሲሆን ወራሾች ኮንዶሚንየም ደርሷቸው ወረዳው ቤቱን ተረክቦ አሽነት በነበረ ጊዜ ጥቅምት 27/2010 ዓ.ም ቤቱን እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቅያ ቢሰጣቸውም ለማስረከብ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡በመሆኑም አመልካቾች በአዋጁ ያልተወረሰ ቤት የያዙ ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካቾች መቃወሚያ አቅርበው ፍርድ ቤቱም መቃወሚያዎቹን መርምሮ ውድቅ በማድረግ ብይን የሰጠ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስም የቤት ቁጥር 159 በአዋጅ ቁ.47/67 መሰረት ተወርሶ መንግስት የሚያስተዳድረው የመንግስት ቤት ነው፡፡ የተወረሰውም ከአቶ ነጋሽ ተፈራ ላይ ሲሆን ቤቱ ለአቶ ኃ/ማሪያም አስራት ተከራይቶ ቆይቶ አሁንም ለሌለ ሰው ተከራይቶ ያለ ነው፡፡ስለዚህ የተጠሪ ክስ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ መርምሮ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪ አለም አቀፍ ድርጅት ሆኖ በሁለቱ መንግስታት ተለይቶ የተሰጠውን ይዞታ የሚያመለክት የአየር ካርታና በዚህ በተለየው ቦታ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች ዝርዝር ያቀረበ መሆኑን፣ተጠሪ ለንብረቱ ካርታ ማቅረብ የማይጠበቅበት መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 21684 ከተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል መሆኑን፣አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ከአቶ አስራት ኃ/ማሪያም ጋር የኪራይ ውል በማድረግ የአስተዳደር አካሉ ኪራይ ሲሰበስብበት የነበረ ቢሆንም አመልካቾች ለተጠሪ ተለይቶ የተሰጠው ይዞታ የለም ይህ ቤትም በዚህ በተለየ ይዞታ ውስጥ አይገኝም በተጠሪም አልተሰራም በማለት ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩና ባለንብረትነትን የሚያፀድቀው የስራና ቤት ሚኒስቴር ለተጠሪ በተሰጠው ክልል ውስጥ ያለ ይዞታና ንብረት ሊወረስ እንደማይችል፣የተወሰደ ይዞታና ንብረት ካለም እንዲመለስለት የተፃፈውን ደብዳቤ በማቅረብ ያስረዳ ስለሆነ አመልካቾች ክርክር የቀረበበትንና በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 159 ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከዓለም አቀፍ ሕግ አንፃር ያቀረቡት ክርክር የፌደራል ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው ሕግ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቅጽ 11(2) መሰረት ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ ሳለ የስር የመጀመሪ ደረጀ ፍርድ ቤት ከፍርድ ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረው የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ አከራካሪው የቤት ቁጥር 159 የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ በመሆኑ አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 መሰረት የከተማ የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ ጠቅሰን ለፍርድ ቤቱ ያቀረብነውን አቤቱታ አልፎ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ ተጠሪ ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ ያቀረበው ቃለ ጉባኤ ፣የአየር ካርታ ፣ዓለም አቀፍ ስምምነት ክርክር ባስነሳው ቤት መብት ያለው ስለመሆኑ ያቀረበው የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሌለበት ባለመብት መሆኑን የሚያሳይ ባልሆነበት የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ተቀብሎ የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ መርህ ያልተከተለና መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊሻር ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 በመንግስት የተወረሰ ስለመሆኑ በተገለፀበትና ተጠሪ የቤቱ ባለቤት ሆነው ለአቶ ነጋሽ ተፈራ ያስተላለፉት ስለመሆናቸው ተረጋግጧል በሚል አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስም አንድ ክርክር በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 11(2)(ሀ) መሰረት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ድርጅቱ አለም አቀፍ ስለሆነ ሳይሆን ጉዳዩ የአለም አቀፍ ህግን የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ በመሆኑ፣የከተማ አስተዳደሩን ፍርድ ቤት ስልጣን አስመልክቶም ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ስልጣን የሚኖረው የከተማው አስተዳር ስለመሆናቸው ክርክር ባልቀረበባቸው የይዞታ፣የኪራይና ተመሳሳይ ክርክሮች ላይ በመሆኑ አመልካቾች ይህንን በተመለከተ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፣አመልካቾች ክርክር የተነሳበትን ቤት አከራይቼ ይኖሩ ነበር ያላቸው አቶ ኃ/ማሪያም አስራት ሲሞቱ ባለቤታቸው ወ/ሮ እቴነሽ ነጋሽ ቤቱ የተጠሪ መሆኑን አውቀው ቤቱን እንድንረከባቸው ለተጠሪ ድርጅት የፃፉትን ደብዳቤ ለስር ፍርድ ቤት አያይዘን አቅርበናል፣ከዚህም በተጨማሪ የተጠሪ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ሊወረሱ እንደማይችሉ የስራና ከተማ ልማት ቤት ሚኒስቴር የፃፈውን ማስረጃ በማቅረብ ክርክራችንን ያስረዳን ስለሆነ ይህም ክርክር የተነሳበት ቤት በሕግ አግባብ ያልተወረሰ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ አመልካቾች የቤት ቁጥር የማይገልጽ ተዓማኒነት የጎደለውን ቅጽ በማቅረብ ቤቱ ተወርሷል ለማስባል ያቀረቡት ማስረጃ እና መከራከሪያ ፍፁም ከእውነት የራቀ እና በሕግ የተደገፈ ስላልሆነ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊያፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡አመልካቾች ከስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን አንፃር ሁለት ክርክሮችን ያቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 11(2) ን መሰረት ያደረገ ሆኖ ተጠሪ ከአለም አቀፍ ህግ አንፃር ያቀረበውን ክርክር የማየት ስልጣኑ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ማስተናገዱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን በመጥቀስ የቀረበ ነው፡፡ተጠሪ በኢትዮጲያና ጅቡቲ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት መሰረት የተቋቋመ የሁለቱም መንግስታት ንብረት የሆነ ድርጅት መሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ ነው፡፡

የግል አለም አቀፍ ህግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 11(2)(ሀ) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር እንዲወድቅ የሚያደርገው መሰረታዊ ጉዳይ ተጠሪ በኢትዮጲያና ጅቡቲ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት መሰረት የተቋቋመ የሁለቱም መንግስታት ንብረት የሆነ ድርጅት መሆኑ ሳይሆን ለክርክር የቀረበው ጉዳይ የሁለቱን ሀገሮች ህጎችን ገፋ ሲልም የአለም አቀፍ ህግን የተፈፀሚነት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡(በተመሳሳይ ጉዳዮች በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 100290፣152590 እና በሌሎች ተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይመለከቷል፡፡)

አሁን በያዝነው ጉዳይ በግራ ቀኙ መሃል የተያዘው ጉዳይ የሁለቱን ሀገሮች ህጎችን አልያም የአለም አቀፍ ህግን የተፈፀሚነት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ በዚህ አግባብም እነዚህ ህጎች ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ የሚፈቱበትን አግባብ መለየትን፣ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ በመፍታት ረገድ በእነዚህ ሀገር ህጎችና አለም አቀፍ ህግ መሃል አለመጣጣም መኖር አለመኖሩን መለየትን፣አለመጣጣም የሚኖር

ከሆነም አለመጣጣሙ የሚፈታበትን አግባብ መለየትን በመጨረሻም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለውን ህግ መምረጥን የሚጠይቅ የክርክር አመራር ሁኔታ ባልተፈጠረበት ከዚህ ይልቅ በግራ ቀኙ መሃል ያለው የመፋለም ክርክር የሌሎች ህጎችን የተፈፀሚነት ጥያቄ የማያስነሳ በሀገራችን የንብረት ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች አግባብ እልባት የሚያገኝ ሆኖ እያለ ተጠሪ በኢትዮጲያና ጅቡቲ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት መሰረት የተቋቋመ የሁለቱም መንግስታት ንብረት የሆነ ድርጅት ስለሆነ ብቻ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 11(2)(ሀ) መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት መከራከራቸው ከላይ በተመለከተው አግባብ ለአዋጁ አንቀፅ 11(2)(ሀ) የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ ሆኖ አስተዳደሩ የሚያስተዳድረው በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41 መሰረት በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ስልጣን ያለው አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ነው በማለት አመልካቾች ከፍርድ ቤቱ ስልጣን ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን መቃወሚያ በተመለከተ በግራ ቀኙ መሃል ያለው ክርክር የቤት ቁጥር 159 የሆነው ቤት ይገባኛል በሚል የቀረበ የመፋለም ክርክር መሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41(1)(ረ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የከተማ አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው የቤቱ ባለቤትነት የከተማው አስተዳደር ስለመሆኑ ክርክር ሳይኖርበት ከባለቤትነት በመለስ የሚነሱ ክርክሮችን አስመልክቶ ነው፡፡(በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 32376፣33841 እና በተመሳሳይ መዝገቦች ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይመለከቷል፡፡)ይህ ከሆነ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ በሚያካሂዱት የመፋለም ክርክር ላይ የዳኝነት ስልጣን አላቸው ሊባል የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ አመልካቾች ከፍርድ ቤቱ የዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን መቃወሚያ አልተቀበልነውም፡፡

ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳዩ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ተጠሪ ለንብረቱ ካርታ ማቅረብ የማይጠበቅበት ህዝባዊ ድርጅት ከመሆኑ አንፃር በሁለቱ መንግስታት ተለይቶ የተሰጠውን ይዞታ የሚያመለክት የአየር ካርታና በዚህ በተለየው ቦታ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች ዝርዝር ያቀረበ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነጥብ ሲሆን ፣ ለተጠሪ ተለይቶ የተሰጠው ይዞታ የለም ይህ ቤትም በዚህ በተለየ ይዞታ ውስጥ አከራካሪው ቤት አይገኝም ቤቱ በተጠሪም አልተሰራም በማለት አመልካቾች ክርክር ባላቀረቡበት፣ይህም አከራካሪው ቤት በተጠሪ የተሠራና ለተጠሪ ተለይቶ በተሰጠው ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ለመሆኑ በአመልካቾች የታመነ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ፣ ባለንብረትነትን የሚያፀድቀው የስራና ቤት ሚኒስቴር ለተጠሪ በተሰጠው ክልል ውስጥ ያለ ይዞታና ንብረት ሊወረስ እንደማይችል፣የተወሰደ ይዞታና ንብረት ካለም እንዲመለስለት የፃፈው ደብዳቤ መቅረቡም ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ላይ ከአመልካቾች የተሻለ መብት ያለው መሆኑን እንዳስረዳ የሚያሳይ በመሆኑ፣ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12(2) መሰረት የከተማ ቤት ባለንበረትነትን በወቅቱ በነበረው አወቃቀር የሚያፀድቀው የስራና ቤት ሚኒስቴር የአዋጁን አንቀፅ 43 በመጥቀስ እና በሁለቱ ሀገሮች መሀከል የተደረገውን ስምምነት በመጥቀስ ለተጠሪ የተሰጠው ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ይዞታና ንብረት ሊወረስ እንደማይገባ ፣የተወሰደ ንብረትና ይዞታ ካለም ሊመለስ እንደሚገባ መግለፁ በስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጡ አመልካቾች አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ የሚያስተዳድሩት መሆኑን በመግለፅና ቅፅ 003 እና ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎችን በማቅረብ በቤቱ ላይ የሚያቀርቡት ክርክር አዋጁንና አዋጁን መሰረት በማድረግ የተፃፈውን የስራና ቤት ሚኒስቴር መግለጫ መሰረት ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ይህም የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን በመስማት በመመርመርና በመመዘን የደረሱበት መደምደሚያ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ህጎች እና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረታዊውን የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ያደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ስለሚያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.60123 በቀን 24/02/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካቾች አከራካሪውንን ቤትን ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.247606 በቀን 17/09/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስለገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ